# የደም ዕምባ ያነቡ የኤርትራ ህጻናት እና ለኢሳያስ ድጋፍ የተሰማራው ባንዳው ግንቦት 7

## ጌታቸው ረዳ (Editor Ethio Semay)




ለበርካታ አመታት በግንቦት 7 ውስጥ የተሰማሩ መሪዎች አብዛኛዎቹ ጸረ አማራ እና ጠባብ ጎሰኞች እንዲሁም የወያኔ አንቀጽ 39 አክባሪዎች መሆናቸው ለብዙ ጊዜ በማስረጃ አስደግፌ ተከራክሬአለሁ። አርቀው የሚያዩ አስተዋይ ሰዎች የዚህ ቡድን መሪዎች ማንነት ገና ቅንጅት ሲፈርስ እና ከመፍረሱ በፊት ስለነቁባቸው፤ የነዚህ ማንነት ለመረዳት ጊዜ አልፈጀባቸውም። እነኚህ ግለሰቦች፤ ለወያኔ ዕድሜ ርዝመት አስተዋጽኦ ያደረጉ እና እንደውም በከፍተኛ የፖለቲካ ቅስቀሳ ክፍል ሃላፊ ሆነው ያገለገሉ እንደ አንዳርጋቸው ጽጌ የመሳሰሉ የወያኔን ፖለቲካና ፖሊሲ ተግባር ላይ እንዲውል፤የቀሰቀሱ፤ ያደራጁ፤ አማራው ሲታረድ ከገዢው መደብ ቆመው ለገዢው ሲያጎበድዱ የነበሩ፤ እንዲሁም ጸረ ኢትዮጵያ አንድነት፤ጸረ አማራና ሰንደቃላማችን የሚወነጅልና የሚያሳንስ መጽሐፍ የጻፉ ‘አለቅላቂዎችና አደገኛ ሰዎች’ አሳዛኝ የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ፤ ነፃ አውጪዎቻችን ናቸው ብለው ወገባቸውን ዳግም ለውርደት ያለጠለጡ አሳፋሪ ምሁራን ሲደግፏዋቸው አይተናል።

ሆኖም የጊዜ ጉዳይ እንጂ በለመዱት የማለቅለቅ ባሕሪ መጓዛቸው እንደማይቀር የተነበይን ሰዎች፤ ዛሬ ትንቢታችን እውን ሆኖ እያየን ነው። የትግርኛው ምሳሌ እንደነገረን “ደርሆ ጻሕቲራ ጻሕቲራ መሕረዲኣ አውጸአት ካራ” (ዶሮ፤ ቧጭራ ቧጭራ፤ አወጣች ከምድር ማረጃዋ ካራ!)። ግንቦት 7 ዘልሎ፤ ዘልሎ መጨረሻ ትክክለኛ ገጽታውና የለመደው የባንዳ ባሕሪው በመከተል፤ ህጻናትን ደም ያስለቀሰ፤ ብዙ ሕዝብ የፈጀ፤ አረመኔው “የሳሕል ጅብ” ኢሳያስ አፈወርቅን በመደገፍ ከሻዕቢያ ደጋፊዎች ጋር ሰልፍ ወጥቶ አይተናል (ይህ

የመጀመሪያ ጊዜው ባይሆንም)። ለዚህ አሳፋሪ ተግባሩም በታሪክ ውስጥ ታይቶ ተሰምቶ የማያውቅ ኤርትራዊያን እራሳቸውን እጅግ ያስገረመ “ኤርትራኖች ምራቃቸውን በግንቦት 7 መሪና በንአምን ዘለቀ ላይ ሲተፉበት የሚያሳይ አሳፋሪ ካርቱን” የተሰራለት የቅጥረኛነት ባሕሪ በየፉስ ቡክ ሲቀባበሉት ለማየት አስችሎናል። ከዚህ ማረን ከማለት ምን ይባላል?




የሳሕሉ አባ ጅቦ ብዙ በረሃ ውስጥ በነበረበት ወቅት የተቃወሙት ታጋዮች በመጥረቢያ ተፈልጠው እንዲሞቱ የፈረደ (በቅርቡ ያደመጥኩት አዲስ አስደንጋጭና ዘግናኝ ቃለ መጠይቅ)፤ እንዲሁም “አለና” በተባለ መጽሐፍም (እኔ ብላሽ ታሕሪር በሚል ጨምቄ ለአማርኛ አንባቢ ያቀረብኩት መጽሐፍ) ሰዎች እንደ ናዚዎቹ በኡቶን (ምጣድ ውስጥ) እስጥ እንደ ዳቦ በእሳት እየተጠበሱ የፍጢኝ ታስረው እየተገፈተሩ እየተቃጠሉ እንዲሞቱ በማድረግ ብዙ ሰው መፍጀቱን ብዙ መጽሐፍቶች፤ ምስክሮች፤ቃለ መጠይቆች፤ ተደርገዋል።

ዛሬም ብሎ፤ ብሎ ወደ ሥልጣን ከወጣም ወዲህ የመጨረሻ ሰለባዎቹ ህጻናት ሆነዋል። በዚህ ምክንያት ደም ያስለቀሳቸው ታዳጊ ህጻናት፤ ኢሳያስ ወደ ዓለም ፍርድ ቤት ይቅረብ ብለው ***በጀኔቫ ብቻ*** **14** ሺሕ ኤርትራዊያን እና በመላው ዓለምም (ሰላማዊ ሰልፍ በማይታወቅባት ከኤርትራ በስተቀር) በየአገሩ ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው በጉንጮቻቸው ላይ የደም ቀለም የተቀባ ዕንባ እያነቡ ለዓለም የድረሱልን እሪታ አስተጋብተዋል።

ከዚህ በታች የሚታዩ ፎቶግራፎች፤ ወጣቶች ጸጉራቸውን በሓዘን መልክ ተላጭተው፤ ወጣት ሴቶችም የሐዘን ጥቁር ልብስ ለብሰው፤ ቀሳውስትና ዲያቆናት እንዲሁም የክርስትና እና እስልምና ተከታይ ምዕመናኖች ሁሉ ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት ኢሳያስ ለፍርድ ይቅረብ ብለው የወጡበት ሰላማዊ ሰልፍ ቀርቧል። ፎቶግራፎችን ከማየታችን በፊት በነገራችን ላይ ግንቦት7 የተካፈሉበትና ለኢሳያስ አፈወርቅ ድጋፍ በመስጠት ፊርማ ያሰባሰቡ ኢትዮጵያዊያን ባንዳዎች እና የሻዕቢያ ደጋፊ ኤርትራዊያን “ጥቂት ወጣቶች/አብዛኛዎቹ ሽማግሌዎች/ስማቸው መጻፍ የማይችሉ ባልቴቶች እና ያልተማሩ ግለሰቦች.....” ሲሉ ተቃዋሚዎቹ ይቀልዱባቸዋል) በጠቅላላ 2000 (ሁለት ሺህ) ብቻ እንደነበሩ ብዙ ተንታኞች እና የቪዲዮ ማስረጃዎች ቀርበዋል።

ኤርትራ በረሃ ውስጥ “የደም ዕምባ” በማስለቀስ የሚከሰሰው ግንቦት 7 በአባላቱ የለመደውና የፈጸመው የዱርየና አረመኔ ሰውን አስሮ የማሰቃየት ሥራ (ይህንን ፎቶግራፍ ኢ.መልከቱ)፤



*Victim of Andargachew Tisge Ginbot 7 fighter in Eritrea explained his ordeal of turture in Eritrea with Tears.*

**ሽታው ሽፈራው ስቃይ እምባ እየተናነቀው እያለቀሰ የተናገረውን ማስረጃ ለማድመጥ እነሆ፤ በሰፊውም በራሴ ኢትዮጵያን ሰማይ ድረገጽም ከ2 አመት በፊት ቀርቧል። Ginbot 7 head of finance Shitaw Shiferraw talks about his ordeal in Eritrea**

## https://youtu.be/XW3kk7Ajhbk

ሳይጠኑ ጎፈሬ እንደተባለው ገና ሥልጣን ከመውጠቱ እና የበረሃ ጉልበቱ ሳያጠናክር የበረሃ ስራው "ሀ" ብሎ ኢትዮጵያዊያንን መግረፍ የጀመረ አስነዋሪው ግንቦት 7 ዛሬ በኢሳያስ ተላላኪ "ዝምብ ካድሬዎችና ውሻ ፖሊሶች" (የያሬድ ጥበቡ አባባል ልዋስና) ደብዳቢዎች እጅ ኤርትራዊያን ህጻናት እና ወጣት ልጃገረዶች የደም እምባ ቢያነቡ ለግንቦት 7 ምኑ ነው? ምንም! ገራፊ ለገራፊ እጅ ለእጅ ተያይዞ ቢደጋገፍ፤ ከገራፊዎች ቡድን የሚጠበቅ ባሕሪ ስለሆነ የግንቦት 7 ባንዳዊ ባሕሪ ለአረመኔው ጥብቅና ቆሞ ባንዳዊ ጩኸት ቢያስጋባ ከማፈር ሌላ ውጤት አያገኝም።

የወጣቶች ደምና ስቃይ እንዲቀጥል የነብሰ ገዳዩ የኢሳያስ ደጋፊ ሆኖ መቆሙ ግን መቸም ቢሆን የግንቦት 7 አሳፋሪ ታሪክ፤ ከወያኔዎች እና ከኦኖጎች ማሕደር ውስጥ አብሮ በደባልነት የሚዘግበው መሆኑን በእርግጠኛነት ልነግራችሁ እችላለሁ። መጨረሻቸውም እንደማያምር ብዙ ጊዜ የተነገረ እውነታ ስለሆነ፤ አብረን ድምዳሜአቸውን እንከታተላለን።

*የደም እምባ አስለቃሽ ገራፊዎች እና የደም እምባ አልቃሾች ፎቶ ይኼው*




*ይመልከቱ!!!!*




ኢሳያስ ኣብ ፍርዲ
ይቕረብ!!


كفى المهانة والإذلال والإستعباد


ኢሰያስ ናብ ፍርዲ ይቅረብ


ግህሰት ሰብኣዊ መሰላት
የብቅዕ!!


Stop Slavery in Eritrea!
ኣብ ኤርትራ ባርነት የብቅዕ!







*ግንቦት 7 የተባለው ከባኮ የወጣ አዲስ ባንዳ የነዚህ ህጻንት እና እስላም ፤ክርስትያን ምዕመናን እንዲሁም እንናቶች እና አረጋዊያን የደም እምባ እንዲቀጥል ቅጥረኛነቱን ለናቅፋው ጅብ ለኢሳያስ አፈወርቂ ጥብቅና ቆሟል። ፍርዱ ታሪክ እንዲመዘግበው ሰነዱን ይኼው አቅርበንለታል።የደም ዕምባ ያለቀሱ የኤርትራ ህጻናት ለኢሳያስ ድጋፍ የተሰማራው ባንዳው ግንቦት 7 በቅጥረኛ ወታደርነትና ተላላኪነት ተጠያቂ አድረገውታል።*

አመሰግናለሁ።

ጌታቸው ረዳ (Editor Ethio Semay) getachre@aol.com